## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር -----/2008

## ስለዱር ሕይወት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የወጣ
## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ---/---- አንቀጽ -- እና በዱር ሕይወት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ---/---- አንቀጽ ----- መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የዱር ሕይወት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ---/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

*2.* ***ትርጓሜ***

*የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፣*

*1/ "አዋጅ" ማለት የዱር ሕይወት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር.... /2008 ነው፣*

2/ በአዋጁ አንቀጽ --- የተሰጡት ትርጓሜዎች ለዚህም ደንብ ተፈጻሚ ይሆናሉ፣

3/ "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ዱር ሕይወት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፣

4/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

### ክፍል ሁለት

### የዱር ሕይወት የጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር

3. **የዱር ሕይወት የጥበቃ ቦታዎች ዳር ድንበር**

የዱር ሕይወት የጥበቃ ቦታዎች ዳር ድንበር በነባሩ የጥበቃ ቦታዎች ዳር ድንበር ላይ የተመሰረተ ወይም ሥርዓት አያያዛቸውን ለማሻሻል በፌደራል መንግሥት ወይም በክልሎች እንደገና ወይም እንደ አዲስ የሚከናወን ክለላን መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡

4. **በፌደራልና በክልል መንግሥት የሚተዳደሩ የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች**

1/ በአዋጁ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 በተደነገገው መስፈርት መሠረት የሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ፣ የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ፣ የነጭ ሣር ብሔራዊ ፓርክ፣ የኦሞ ብሔራዊ ፓርክ፣ የአብያታ ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ፣ አዋሽ ብሔራዊ ፓርክ፣ ስንቀሌ የቆርኬዎች መጠለያ፣ ባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ፣ ጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ፣ አልጣሽ ብሔራዊ ፓርክ፣ ቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክ፣ ገራይሌ ብሔራዊ ፓርክ እና የሃላይደጌ አሰቦት ብሔራዊ ፓርክ በባለሥልጣኑ የሚተዳደሩ ይሆናሉ፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ ስልጣኑን በውክልና አግባብ ላላቸው የክልል አካላት ሊሰጥ ይችላል፡፡

DRAFT

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከቱት ውጭ የሆኑ የዱር ሕይወት የጥበቃ ቦታዎች በክልሎች፣ በአካባቢው ሕብረተሰብ፣ በግል ባለሃብቶች ወይም በዱር ህይወት ጥበቃ የተሰማሩ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚተዳደሩ ይሆናሉ፡፡

## 5. <u>በብሔራዊ ፓርኮች፣ በዱር ሕይወት መጠለያዎችና በዱር ሕይወት ጥብቅ ክልሎች ውስጥ እንዳይከናወኑ ስለተከለከሉ ተግባራት፣</u>

1/ በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከተው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ማኛውም ሰው በብሔራዊ ፓርክ ወይም የዱር ሕይወት መጠለያ ክልል ውስጥ ቀጥሎ የተመለከቱትን ድርጊቶች መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡

ሀ) ማናቸውንም የጦር መሣሪያ ይዞ መገኘት ወይም ማስተላለፍ፤

ለ) ማደን ወይም ዓሣ ማጥመድ፤

ሐ) ከተፈቀደው ቦታና ፍጥነት ውጪ ማሽከርከር፣ የአየር መንኮራኩር ወይም ጀልባ ማንቀሳቀስ፤

መ) ማናቸውንም ተፈጥሮአዊ ወይም ሰው ሠራሽ ነገር ማንሣት፣ ማወክ፣ ማበላሸት ወይም ማጕሳቆል፤

ሠ) የግብርና ሥራ ማካሄድ ወይም መሬት ለእርሻ ተግባር ማዘጋጀት፣

ረ) የቤት እንስሳትን ለግጦሽና ለውሃ ማሠማራት፤

ሰ) ማናቸውንም የቤት እንስሳትን ወይም የዱር እንሰሳትን ወደ ቦታው ማስገባት፣ ማሳለፍ ወይም እንዲሠማራበት ማድረግ፤

ሸ) የማዕድን ፍለጋ ወይም ቁፋሮ ማካሄድ፤

ቀ) ማናቸውንም እፅዋት መትከል፣ መቁረጥ፣ መፍለጥ፣ ማንሣት፣ መውሰድ፤ ማበላሸት ወይም ማስተላለፍ፤

በ) እሳት ማቀጣጠል ወይም ለማቀጣጠል ሙከራ ማድረግ፤

ተ) የንብ እርባታ ማካሄድ፣ ማር መቁረጥ ወይም የዱር ሕይወት ውጤት መውሰድ ወይም ለመውሰድ መሞከር፤

ቸ) የመንገድ ወይም የሌላ ግንባታ ሥራ ማካሄድ ወይም ነባሩን የተፈጥሮ አቀማመጥ ማበላሸት ወይም መረበሽ፤

ኀ) ማናቸውንም ፀረ-ተባይ ወይም ፀረ-አረም ኬሚካል መጠቀም፤ መርጨት፣ መጣል ወይም ይዞ መገኘት፤

ነ) ማንኛውም እቃ መሸጥ ወይንም ለሽያጭ ማቅረብ ወይም አገልግሎት መስጠት፣

ኘ) ማንኛውንም መግለጫ ወይም ማስታወቂያ መለጠፍ፤

አ) አስፈላጊው የአዋጭነትና ሁሉን አቀፍ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ጥናት ሳይከናወንና በሚመለከተው አካል ሳይጸድቅ ማንኛውንም የልማት ተግባር ማካሄድ፤

ከ) ፍቶግራፍ በማንሳት እና ከአየር ወይም ከምድር ፊልም በመቅረጽ ለንግድ ማዋል፤

DRAFT

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል መንግሥት አካል በጽሁፍ በሚፈቅደው መሠረት ቀጥሎ የተዘረዘሩት ድርጊቶች በብሔራዊ ፓርክ ወይም በዱር ሕይወት መጠለያ ውስጥ ሊከናወኑ ይችላሉ፤

ሀ) የተፈቀደላቸው አስጎብኚችና ቱሪስቶች ወደ ብሔራዊ ፓርክ ወይም የዱር ሕይወት መጠለያ ውስጥ ለመግባትና ለመቆየት እንዲሁም በዚህ ደንብ መሠረት በወጣ መመሪያ የተፈቀዱ ድርጊቶች ለመፈጸም ይችላሉ፡፡

ለ) የተፈቀደላቸው ባለሙያ ፎቶግራፍ አንሺዎች፣ ደራሲዎችና ሠዓሊዎች ወደ ብሔራዊ ፓርክ ወይም የዱር ሕይወት መጠለያ ውስጥ ለመግባትና ለመቆየት እንዲሁም በየሙያቸው የሚፈልጉትን ተግባር ለማከናወን ይችላሉ፤

ሐ) ሥልጣን የተሰጣቸው ሠራተኞች ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ከነቤተሰቦቻቸው ወደ ወደ ብሔራዊ ፓርክ ወይም የዱር ሕይወት መጠለያ ውስጥ ለመግባትና ለመኖር ይችላሉ፤

መ) ሥልጣን የተሠጣቸው ሠራተኞችና የተፈቀደላቸው ተመራማሪዎች በዚህ ደንብና ደንቡን መሠረት አድርገው በወጡ መመሪያዎች መሠረት የዱር ሕይወት ሀብት ውጤትን መውሰድ፤፣ እጽዋት መቁረጥ ወይም ማቃጠል፣ ተሽከርካሪዎች ማንቀሳቀስና የግንባታ ሥራ ማካሄድ ይችላሉ፤

ሠ) በብሔራዊ ፓርኮች እና በዱር ሕይወት መጠለያዎች አካባቢ በሚኖረው ሕብረተሰብና በፓርኩ ወይም መጠለያው አስተዳደር መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት እንደ ንብ ማነብና ማር የመቁረጥ፣ ሣር አጭዶ የመውሰድ እና ለባህላዊ መድኃኒት የሚውል ዕፅዋት የመሰብሰብ ተግባራት ቁጥጥር እየተደረገባቸው እንዲከናወኑ ሊፈቀዱ ይችላሉ፡፡

ረ) የማዕድን ፍለጋና ሌሎችም የልማት ሥራዎች አስፈላጊ ሁነው ሲገኙ ከዱር ሕይወት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ተግባራት ጋር ተጣጥመው ሊከናወኑ ይችላሉ፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል መንግሥት አካል፤

ሀ) በዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታ ውስጥ ለሥራ የተሠማሩ የመንግሥት ሠራተኞች ከነቤተሰቦቻቸው እና ሳይንሳዊ ምርምር የሚያካሂዱ ሰዎች በዱር ሕይወት ጥብቅ ክልሉ ውስጥ በጊዜያዊነት ለመኖር እንዲችሉ፣ እና

ለ) ሥፍራው የዱር ሕይወት ጥብቅ ክልል ከመሆኑ በፊት በቦታው ላይ ሠፍረው የነበሩት ሰዎች በዚያው መኖር እንዲችሉ፣ መፍቀድ ይችላል፡፡

4/ በዱር ሕይወት ጥብቅ ክልል ውስጥ ለመኖር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) መሠረት የተፈቀደላቸው ሰዎች በክልሉ ውስጥ የቀድሞ ይዞታቸውን ሳያስፋፉ ከብቶቻቸውን ለማስጋጥና ውሃ ለማጠጣት እና ንብ ለማርባት ይችላሉ፡፡ ሆኖም የዱር ሕይወት ጥበቅ ክልሉን የሚያስተዳድረው አካል ክልሉን ለማሳደግ ሲወስን ሌላ ምትክ ቦታ ተዘጋጅቶላቸው እንዲሰፍሩ ይደረጋል፡፡

DRAFT

6. <u>የዱር እንስሳትን ስለማደን</u>

1/ በዚህ ደንብ መሠረት የቁጥጥር አደን ቀበሌውን በመጥቀስ በሚሰጥ ፈቃድ መሠረት ካልሆነ በስተቀር በቁጥጥር በሚታደንበት ቀበሌም ሆነ በአካባቢ ህብረተሰብ የዱር ሕይወት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ቦታ ወይም በሌላ ማናቸውም የዱር ሕይወት መኖሪያ ቦታ ማደን የተከለከለ ነው፡፡

2/ የባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው ክልል የአደን ተቆጣጣሪ በሌለበት አደን ማከናወን የተከለከለ ነው፡፡

3/ ክልሎች እና ባለሥልጣኑ የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን ዳር ድንበር በመከለል በግልጽ ጨረታ አወዳድረው ለአሳዳኝ ድርጅቶች ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በኮንሴሽን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

4/ ለአንድ አሣዳኝ ድርጅት በኮንሴሽን በተሠጠ የቁጥጥር አደን ቀበሌ ውስጥ ከባለይዞታው ስምምነትና ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ውጪ ሌላ አሣዳኝ ድርጅት እንዲያሣድን አይፈቀድለትም፡፡

5/ የአሣዳኝ ድርጅት ፈቃድ በየዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ 30 ባሉት ቀናት ውስጥ መታደስ አለበት፡፡

6/ የቁጥጥር አደን ቀበሌ ኮንሴሽን ስምምነት ከሚከተሉት ምክንያቶች ባንዱ ሊቋረጥ ይችላል፤

ሀ) ለተጨማሪ ጊዜ ካልተራዘም በስተቀር የኮንሴሽን ዘመኑ ሲያበቃ፣

ለ) አሣዳኝ ድርጅቱ ያልተፈቀደለትን ወይም ከተሰጠው ኮታ በላይ የዱር ሕይወት አሣድኖ ከተገኘ፤

ሐ) አሣዳኝ ድርጅቱ በኮንሴሽን ስምምነቱ መሠረት መክፈል የሚገባውን ዓመታዊ ክፍያ በወቅቱ ሳይፈጽም ከቀረ፤

መ) አሣዳኝ ድርጅቱ የኮንሴሽን ስምምነቱን ግዴታዎች በተለይም በያዘው የቁጥጥር አደን ቀበሌ ውስጥ ለተፈጥሮ ሀብት መደረግ ያለበትን እንክብካቤ ካላደረገና ግዴታዎቹን ሳያከብር ከቀረ፡፡

7/ በቁጥጥር አደን ቀበሌነት የሚከለሉ ቦታዎች በሰው ሠራሽ ተጽእኖዎች ያልተጎዱ እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚፈለጉ ሆነው ስፋታቸው ከ100 /አንድ መቶ/ ካሬ ኪሎ ሜትር ማነስ ወይም ከ500 /አምስት መቶ/ ካሬ ኪሎ ሜትር መብለጥ የለባቸውም፡፡

8/ /አምስት መቶ/ ካሬ ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት በላይ ያለው ልዩነት ከ100 /አንድ መቶ/ ካሬ ኪሎ ሜትር በታች ከሆነ በአንድ ላይ ተጠቃሎ የቁጥጥር አደን ቀበሌ የሚሆን እና ለተጨማሪው ካሬ ኪሎ ሜትር በኮንሴሽኑ ስሌት መሰረት ተጨማሪ ክፍያ የሚያስከፍል ሆኖ፤ የቆዳው ስፋት ልዩነት 100 /አንድ መቶ/ እና ከ100 /አንድ መቶ/ ካሬ ኪሎ ሜትር በላይ ከሆነ ግን እንደ አዲስ የቁጥጥር አደን ቀበሌ ተቋቁሞ በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት ለባለሀብት ይሰጣል፡፡

9/ ማንኛውም አሣዳኝ ድርጅት የያዘውን የቁጥጥር አደን ቀበሌ በአግባቡና በዘለቄታዊነት ባለመጠቀሙ ምክንያት የያዘው የቁጥጥር አደን ቀበሌ የሀብት መራቆት ወይም መመናመን በክልሉና በባለሥልጣኑ ክትትልና ጥናት ከተረጋገጠ ባለይዞታነቱ ተሰርዞ የቁጥጥር አደን ቀበሌው እንዲያገግም ይደረጋል፡፡

DRAFT

10/ በቁጥጥር አደን ቀበሌዎች ዳር ድንበር መካከል የ5 (አምስት) ኪሎ ሜትር ደጀን ወይም ነፃ መሬት መኖር አለበት፡፡

11/ የቁጥጥር አደን ቀበሌዎች ከብሔራዊ ፓርኮችና ዱር ሕይወት መጠለያዎች በሚዋሰኑባቸው ዳር ድንበሮች መካከል የ8 (ስምንት) ኪሎ ሜትር ደጀን ወይም ነፃ መሬት መኖር አለበት፡፡

12/ የዱር እንስሳቱን የአደን ተፈላጊነት መሰረት በማድረግ የተለያየ ምድብና ምደባውን መሰረት ያደረገ የአደን የቆይታ ጊዜ ይኖራቸዋል፤

13/ አሳዳኙ የአደን ፈቃድ ቅፅ ሞልቶ እንዲታደኑ ከተፈቀዱለት በተጨማሪ ሌላ ታዳኝ የዱር እንስሳት ለማደን ጥያቄ ሲያቀርብ በተጨማሪ የሚታደነውን የዱር እንስሳ ዋጋና የዋጋውን 15 በመቶ ለባለሥልጣኑ ይከፍላል፡፡

14/ በባለሥልጣኑ በአደን ፈቃዱ ያልተካተተ ሰው በአደን ቦታ ይዞ የተገዘ አሳዳኝ ድርጅት ላይ በአደን ቦታው ለሚቆይበት ጊዜ ለያዘው ተጨማሪ ሰው በነፍስ ወከፍ በደንቡ ሠንጠረዥ ሦስት ተራ ቁጥር 36 የተመለከተውን ክፍያ በየቀኑ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## 7. <u>የአካባቢ ሕብረተሰብ የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች</u>

1/ የአካባቢ ሕብረተሰብ የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎችን ያስተዳድራል፣ ያለማል፣ ይጠቀማል፡፡

2/ የአካባቢ ሕብረተሰብ በኢኮቱሪዝም ሥራዎች ይሳተፋል፣ የሚገኘውን ገቢ ለሕብረተሰቡ ጥቅም ያውላል፡፡

3/ የአካባቢው ሕብረተሰብ ዓመታዊ የአደን ኮታን በባለሥልጣኑ በማፀደቅ በሥሩ በሚተዳደሩት የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሚገኙትን የዱር እንስሳት ለሕጋዊ አዳኝ ይሸጣል፡፡ ገቢውም የሕብረተሠቡ የልማት ክፍተቶችን ለመሙላት ይውላል፤ የማህበረሰቡ ተጠቃሚነት አፈጻጸም በተመለከተ በዝርዝር ሕጎች ይወሠናል፡፡

4/ የአካባቢው ሕብረተሰብ፣

ሀ) የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታውን ለማሻሻል የሚረዱ የልማት ሥራዎችን ከራሱ ወይም ከሌሎች ምንጮች በሚገኝ ገቢ ያከናውናል፣

ለ) ለዱር ሕይወት ጥበቃ የሚያግዙ ሠራተኞችን ያስለጥናል፤

ሐ) የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታውን የተፈጥሮ ሀብት ይዘት የማይጐዱ የልማት ሥራዎችን ያከናውናል፤

መ) የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታውን ልማት ለማጠናከር የገንዘብና የጉልበት አስተዋጽኦ ያደርጋል፤

ሠ) በዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታው ውስጥ የሚከናወነውን የአጠቃቀም ዓይነት ከሚመለከተው የክልሉ አካል ጋር በመመካከር ይወሰናል፡፡

## 8. <u>የዱር ህይወትና መኖሪያ አካባቢያቸውን መልሶ ሰለማበልጸግ</u>

DRAFT

1. ባለሥልጣኑ በሰው ሰራሽ እና ተፈጥሮ ጫና ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው የዱር ህይወት ጥበቃ ቦታዎች ላይ ተገቢው ጥናት በማካሄድ እንዲያገግሙ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
2. ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በዱር ህይወት ጥበቃ ቦታዎች መልሶ ማበልጸግ ሂደት ከቦታቸው ለሚነሱ የህብረተሰብ አካላት አማራጭ የኑሮ ዘዴ እንዲፈጠርላቸው ያደርጋል፡፡
3. ባለሥልጣኑ ወጥነት ያለው የወራሪ አረም አወጋገድና የዱር ህይወት መኖሪያ አካባቢ ሥርአተ-አያያዝ ሰርዓት ይኖረዋል፡፡
4. ባለሥልጣኑ ለዱር እንስሳቱ ጥበቃ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የተለያዩ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ከቦታ ቦታ በማዘዋር እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለፈቃዶች

### 9. የፈቃድ አስፈላጊነት

በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ያልተሰጠው ሰው ማንኛውንም ዓይነት የዱር ሕይወት ለማደን ወይም በህይወት ለመያዝና ለማርባት፣ የዱር ሕይወት ውጤቶች ለመውሰድ፣ በዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥም ሆነ ውጭ የዱር ሕይወትን በፊልም ለመቅረጽ ወይም በዱር ሕይወትና አካባቢያቸው ላይ ጥናት ለማካሄድና የዱር ህይወት ሃብትን በማንኛውም ሁኔታ ጥቅም ላይ ለማዋል አይችልም፡፡

### 10. የፈቃድ ቅድመ ሁኔታዎች

1/ ፈቃድ እንዲሰጠው ከማመልከቱ በፊት በነበሩት አምስት ዓመታት ውስጥ የዱር ሕይወት ጥበቃ ሕግን በመተላለፍ ጥፋት ፈጽሞ የተፈረደበት ወይም የተሰጠው ፈቃድ የተሠረዘበት ሰው በዚህ ደንብ መሠረት ለሚሰጥ ማንኛውም ዓይነት ፈቃድ ብቁ አይሆንም፡፡
2/ እድሜው 18 ዓመት ያልሞላ ወይም የአካል ብቃቱና ጤንነቱ በባለሙያ ያልተረጋገጠ ማንኛውም ሰው ለባለሙያ አሣዳኝነት ፈቃድ ብቁ አይሆንም፡፡
3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ፡፡
4/ በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰጥ ማንኛውንም ዓይነት ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው ማመልከቻውን እንደአግባቡ ባለሥልጣኑ ለዚሁ ተግባር ባዘጋጀው ፎርም ላይ ሞልቶና የፈቃድ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላቱን ከሚያሳዩ ማስረጃዎች ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

### 11. ፈቃድ ስለመስጠት

1/ በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 4 መሠረት የቀረበ የፈቃድ ማመልከቻ ተቀባይነት ሲያገኝ አመልካቹ ተገቢውን የፈቃድ ክፍያ እንዲፈጽም ተደርጎ የጠየቀው ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

DRAFT

2/ ማንኛውም ፈቃድ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎችና በፈቃዱ ላይ የሠፈሩትን ግዴታዎችና ገደቦችን በመጠበቅ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 12. ፈቃድን ስለማሳደስ

1/ ማንኛውም ፈቃድ በየዓመቱ ከሐምሌ አንድ እስከ 30 ባሉት ቀናት ውስጥ መደበኛው የፈቃድ ክፍያ ወይም ከዚያ በኋላ ተጨማሪ ክፍያ ተፈጽሞ መታደስ አለበት፡፡

2/ የፈቃድ እድሳት ማመልከቻ ፈቃዱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 መሠረት መታገድ ወይም መሠረዝ ያለበት ከሆነ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

3/ ማንኛውም ባለፈቃድ የዓመቱን አስፈላጊ የመንግሥት ግብር ስለመክፈሉ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 13. የፈቃድ ክፍያ

1/ በዚህ ፈቃድ መሠረት የሚሰጡ ፈቃዶችን ለማውጣት ወይም ለማሳደስ የሚጠየቁ ክፍያዎች በዚህ ደንብ ሠንጠረዥ ሁለት በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

2/ ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱን ለማሳደስ፣

ሀ) እስከ ነሐሴ 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ዘግይቶ ከቀረበ የማሳደሻ ክፍያውን 30% በተጨማሪነት ይከፍላል፡፡

ለ) ከነሐሴ 30 ቀን በኋላ ዘግይቶ ከቀረበ የማሳደሻ ክፍያውን 50% በተጨማሪነት ይከፍላል፡፡

## 14. የአደን ክፍያና የዱር ሕይወት አጠቃቀም ዋጋ ተመን

1. ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ መሠረት ባለሥልጣኑ የአደን፣ የጉብኝት፣ በሕይወት ንግድ እንዲሁም ከልዩ ልዩ ክፍያ ገቢ ይሠበስባል፤ በሰንጠረገሮቹ ላይ ያልተመለከቱ የዱር ሕይወትን በሚመለከት የሚጠየቅ ክፍያ ባለሥልጣኑ ዓለም አቀፍ ሁኔታን መሰረት በማድረግ ዋጋቸውን ይተምናል፡፡
2. የብሔራዊ ፓርኮችና የዱር ሕይወት መጠለያዎች የጎብኝዎች መግቢያ ዋጋ ተመን በሚመለከት የብዝሃ ህይወት ስብጥርና ክምችትን፣ ቱሪስት ፍሰትን እና የመሰረተ ልማት አቅርቦትን መሰረት በማድረግ በሚወጣላቸው ደረጃ መሰረት ገቢ ይሰብስባል፡፡
3. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ በተቀመጠው መሠረት ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በየሦስት ዓመቱ በመፈተሽ የደረጃና የዋጋ ተመንን በማሻሻል ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባር ላይ ያውላል፡፡
4. በንዑስ አንቀፅ 3 ላይ በተቀመጠው መሠረት በሚኒስቴሩ ፀድቆ የሚወጣው የዋጋ ተመን ከፊልም ቀረፃ እና የጥናትና ምርምር ተግባር በስተቀር የሌሎቹ ዋጋ

DRAFT

ተመን በዚህ በተሻሻለው ደንብ ከተቀመጠው የዋጋ ተመን ያነሠ ለመሆን አይችልም፡፡

5. በዚህ በተሻሻለው ደንብ የተቀመጠው የኮንሴሽን ተመን እንደተጠበቀ ሆኖ አሳዳኝ ድርጅቱ በየዓመቱ ፈቃዱን ሲያድስ በተሠጠው የአደን ኮታ ልክ በእያንዳንዱ ታዳኝ ሕይወት ዋጋ ላይ 5% ተጨማሪ ክፍያ ይፈፅማል፡፡
6. ማንኛውም አሣዳኝ ድርጅት በአንድ ጊዜ የስፖርት አደን ፈቃድ በሚታደነው የዱር እንስሳ ካሊቨር ነፍስወከፍ ከ6 /ስድስት/ በላይ ማደኛ ጥይት ለማስገባት አይችልም፡፡
7. በንዑስ አንቀፅ 6 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በነፍስ ወከፍ ታዳኝ የዱር እንስሳት ከስድስት ጥይት በላይ ለማስገባት የተጠየቀ እንደሆነ ለእያንዳንዱ ጥይት 5 /አምስት/ የአሜሪካን ዶላር የሚከፍል ሆኖ፣ የተጨማሪው የጥይት ብዛት በነፍወከፍ ታዳኝ የዱር እንስሳት ቁጥር ከአራት በላይ መሆን የለበትም፡፡
8. የዱር እንስሳት ለማደን የተፈጸመ የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ አይሆንም፡፡
9. አሳዳኝ ድርጅቶች በውጪ ለሚገኙ ወኪሎቻቸው የሚፈጽሙት ክፍያ ከቱሪስት አዳኙ ከሚያገኙት የቀን ክፍያ ከ15 በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡
10. አሳዳኝ ድርጅቶች በውጪ ለሚገኙ ወኪሎቻቸው የሚከፍሉት ከ15 በመቶ ያልበለጠ ክፍያ የአብሮ ተጓዦችን የቀን ክፍያ አያካትትም፡፡ የአብሮ ተጓዦች የቀን ክፍያ ሙሉ በሙሉ ሀገር ውስጥ ለሚገኙ የአሳዳኝ ድርጅቶች ገቢ መደረግ አለበት፡፡

## 15. <u>ፈቃድ ይዞ ስለመገኘት</u>

1/ ማንኛውም ሰው ፈቃድ የተሰጠበትን ተግባር በሚያከናውንበት ጊዜ ፈቃዱን ይዞ መገኘት አለበት፡፡

2/ ማንኛውም ባለፈቃድ ያደናቸውን የዱር ሕይወት የሚመለከት መረጃ የፈቃዱ የአገልግሎት ጊዜ እንዳለቀ ወይም ባለፈቃዱ ኢትዮጵያን ለቆ በሚሄድበት ጊዜ የአደን ቅጹን ከነፈቃዱ ለሰጠው አካል ያስረክባል፡፡

3/ ባለፈቃዱ ያደነውን የዱር እንስሳት ውጤት ከሥፍራው ከማንቀሳቀሱ በፊት በአደን ቅጹ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡ የዱር እንስሳው ቆስሎ ያመለጠ ከሆነም ይኸው ሁኔታ በዝርዝር በአደን ቅጹ ውስጥ መመዝግብ አለበት፡፡

## 16. <u>ስለተገደሉ ወይም ስለቆሰሉ የዱር እንስሳት</u>

1/ የአደን ፈቃድ የያዘ አዳኝ በማንኛውም ሁናቴ የገደለው ወይም ያቆሰለው የዱር እንስሳት በአዳኙ ላይ ይቆጠርበታል፡፡

2/ የአደን ፈቃድ የያዘ አዳኝ ወይም አሳዳኝ ድርጅት፣

ሀ) ከተወሰነው የማርጣ መጠን በታች የሆነ የዱር ሕይወት አድኖ ከተገኘ የሕይወትውን የነፍስ ወከፍ ዋጋ በእጥፍ ይከፍላል፣

ለ) ሴት የዱር እንስሳ አድኖ ከተገኘ የወንዱን የነፍስ ወከፍ ዋጋ እጥፍ ይከፍላል፡፡

ሐ) ፈቃድ ከተሰጠው የአደን ቦታ ውጭ አሳድኖ ቢገኝ ያደነውን የዱር እንስሳ የአደን ዋጋ እጥፍ ይከፍላል፡፡

## 17. ፈቃድ ስለማስተላለፍ

1/ ማንኛውም ሰው የተሰጠውን ፈቃድ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ወይም የራሱ ባልሆነ ፈቃድ ሊጠቀም አይችልም፣ ሆኖም አዳኝ ቱሪስት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አደኑን ማከናወን ካልቻለ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በአደን ክፍያው ላይ 25% ተጨማሪ ገንዘብ በመክፈል ፈቃዱን ለህጋዊ ወኪሉ ማስተላለፍ ይችላል፡፡

2/ የአደን ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የአደን ወቅቱን ሳይጀምር ወይም ሳያጠናቅቅ አደን ቢያቋርጥ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንደገና አደኑን ያለተጨማሪ ክፍያ ማካሄድ ይችላል፡፡

## 18. ፈቃድን ስለማገድና ስለመሰረዝ

1/ ማንኛውም ባለፈቃድ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም የፈቃዱን ግዴታዎች ጥሶ ሲገኝ ኃላፊነት የተሰጠው የፈቃድ ሰጪው አካል ፈቃዱን ማገድ ይችላል፡፡

2/ ይህን ደንብ በመተላለፍ በፈጸመው ጥፋት ተከስሶ የተፈረደበት ማንኛውም ሰው ፍርድ ቤቱ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በስተቀር የተሰጠው ማንኛውም ፈቃድ ወዲያውኑ እንደተሠረዘ ይቆጠራል፡፡

3/ ፈቃድ የተሠረዘበት ሰው የፈቃዱን ወረቀት በአስር ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ለሰጠው አካል መልሶ ማስረከብ አለበት፡፡

## 19. የውጪ ቱሪስት የአደን ፈቃድ

1/ የውጪ ቱሪስት የአደን ፈቃድ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ 5 ላይ የተመለከቱትን የዱር እንስሳት ለማደን ለውጪ ቱሪስት አዳኞች በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

2/ በአንድ የውጪ ቱሪስት አደን ፈቃድ ሊታደኑ የሚችሉ ታዳኝ የዱር እንስሳት ብዛት ፈቃዱን በሚሰጠው አካል ለበጀት ዓመቱ በሚያፀድቀው ኮታ መሠረት ሆኖ ከየዝርያው አንድ የዱር እንሰሳ ብቻ ይሆናል፡፡

3/ የቱሪስት የአደን ፈቃድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ወር ጊዜ የጸና ይሆናል፡፡

4/ በዱር ሕይወት ሃብቱና የመኖሪያ አካባቢው ዙሪያ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በየጊዜው በማጥናት በሠንጠረዥ 4 ከተመለከቱት የዱር እንስሳት ዝርዝር ላይ ሊቀነስ ወይም ሌላ ያልተካተተ ዝርያ ካለ ሊጨመር ይችላል፡፡

## 20. የአገር ውስጥ ነዋሪ አደን ፈቃድ

1/ የአገር ውስጥ ነዋሪ የአደን ፈቃድ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ 5 ላይ የተመለከቱትን የዱር ሕይወት ለማደን በኢትዮጵያ ውስጥ

ለሚኖሩ የውጪ አገር ዜጎች ወይም ለኢትዮጵያውያን በሚመለከተው የክልል አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

2/ የሀገር ውስጥ ነዋሪ አደን ፈቃድ ጸንቶ የሚቆየው ለአንድ ወር ይሆናል፡፡

21. **<u>የአእዋፍ አደን ፈቃድ.</u>**

1/ የአእዋፍ አደን ፈቃድ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ 7 የተመለከቱትን አእዋፍ ለማደን በሚመለከተው የክልል አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

2/ የአእዋፍ አደን ፈቃድ ከተሰጠው ቀን ጀምሮ ለአንድ ወር የፀና ይሆናል፡፡

3/ የአደን አካባቢዎችን የዝናብ ሥርጭትና የአእዋፍ መራቢያ ወቅትን ግምት ውስጥ በማስገባት፤

ሀ) ለመካከለኛ የሀገሪቱ ከፍተኛ ቦታዎች ከሰኔ 1 ቀን እሰከ ሕዳር 30 ቀን፣

ለ) ለደቡብና ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ከመጋቢት 1 ቀን እስከ ነሐሴ 30 ቀን፣ የአእዋፍ አደን ዝግ ይሆናል፡፡

4/ ከላይ በንኡስ አንቀጽ 3 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ህልውናቸው እጅግ ለአደጋ የተጋለጡ የአእዋፍ ዝርያዎች መኖሪያ አካባቢ ላይ የአእዋፍ አደን ማከናወን የተከለከለ ነው፡፡

22. **<u>የፎፍዬ አደን ፈቃድ</u>**

1/ የፎፍዮ አደን ፈቃድ ለቱሪስት አዳኞች ወይም ለሀገር ውስጥ አዳኞች በሚመለከተው የክልል አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

2/ ለአደን የሚፈቀዱት የፎፍዬ ዝርያዎች ትልቁ ፎፍዬና ተራው ፎፍዬ ብቻ ይሆናሉ፡፡

3/ የፎፍዬ አደን ከነሐሴ 1 ቀን እሰከ ጥቅምት 30 ቀን ብቻ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

23. **<u>ለሳይንስ ጥናት የሚሰጥ ልዩ የአደን ፈቃድ</u>**

1/ ማንኛውንም የዱር እንስሳ ለሳይንሳዊ ምርምር አገልግሎት እንዲውል በሚያስፈልግበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በጥናት ላይ የተመሰረተ ልዩ የአደን ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2/ ልዩ የአደን ፈቃድ ጸንቶ የሚቆየው በፈቃዱ ላይ ለተወሰነው ጊዜ ይሆናል፡፡

3/ ልዩ የአደን ፈቃድ የተሰጠው ሰው የተፈቀደለትን የዱር እንስሳ ለማደን የሚያስችል በቂ ችሎታ የሌለው ከሆነ ከባለሥልጣኑ በሚመደብ ባለሙያ እገዛ አማካይነት ማደን አለበት፡፡

24. **<u>የዱር ሕይወት የመያዝ ፈቃድ</u>**

1/ የዱር ሕይወት የመያዝ ፈቃድ የሚሰጠው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 10 ላይ የተመለከተው የዱር እንስሳት በህይወት ንግድ ለማከናወን ይሆናል፡፡

2/ ባለሥልጣኑ የዱር እንስሳት የመያዝ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት አመልካቹ የዱር እንስሳትን ከነነፍሳቸው ለመያዝና ለማቆየት ያለውን ልምድ፣ የሚይዘው የዱር

DRAFT

እንስሳ ለምን እንደተፈለገ፣ የሚያዝበትን ዘዴና ወደተፈለገበት ቦታ ለማድረስ የሚጠቀምበትን መንገድ የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያቀርብ ማድረግ አለበት፡፡

3/ የዱር እንስሳት የመያዝ ፈቃድ ጸንቶ የሚቆየው በፈቃዱ ላይ ለተመለከተው ጊዜ ይሆናል፡፡

4/ የዱር እንስሳቱ በሚያዝበት ጊዜ ወይም ከዚያ በኋላ ቢሞት በባለፈቃዱ ላይ ይቆጠርበታል፡፡

5/ የዱር ሕይወት የመያዝ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የተፈቀደለትን የዱር እንስሳ ለመያዝ በብረት ወጥመድ፣ በመርዝ ወይም በመርዛማ መሣሪያ መጠቀም ወይም የራሱን ወይም የሌላውን ሰው ሕይወት ለማዳን ካልተገደደ በቀር በማናቸውም የዱር እንስሳት ላይ መተኮስ አይችልም፡፡ ሆኖም በፈቃድ ሰጪው አካል ሲፈቀድለት በማደንዘዣ ጠብመንጃ መጠቀም ይችላል፡፡

6/ ማንኛውም የተያዘ የዱር እንስሳ በሰው ወይም በንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ባለፈቃዱ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 25. <u>ለአደን የተከለሉ የዱር እንስሳት</u>

ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 11 እና 12 ላይ የተዘረዘሩትን የዱር ሕይወት በዚህ ደንብ አንቀጽ 22 መሠረት ካልሆነ በቀር ማደን ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡

## 26. <u>ስለተከለከሉ የማደኛ ዘዴዎች</u>

1/ ማንኛውንም ሰው የዱር እንስሳት ለማደን በሚከተሉት ዘዴዎች መጠቀም የተከለከለ ነው፤

ሀ) ከሁለት መቶ ሜትር ባነሰ ርቀት በተሽከርካሪ፣ በጀልባ ወይም አውሮፕላን ወደ ዱር ሕይወት መጠጋት፤

ለ) እሳት ማስነሳት ወይም የዱር ሕይወትን በእሳት ማባረርና መክበብ፤

ሐ) ከታዳኝ የሌሊት ተንቀሳቃሽ የዱር ሕይወት በስተቀር በጨለማ ማደን፣፤

መ) ከወፍ በቀር ማንኛውንም የዱር ሕይወት በውሻ ማደን፤

ሠ) የክበቡ ስፋት ስምንት ሴንቲ ሜትር ወይም ከዚህ በላይ ስፋት ያለው ወጥመድ ወይም ተመሳሳይ የሆነ በሽቦ በተሠራ ወጥመድ መጠቀም፤

ረ) በተጠመደ ጠብመንጃ፣ በጉድጓድ፣ በቦይ፣ በመረብ፣ በአጥር፣ በወጥመድ፣ በመርዝ ወይም ይህን በመሠለ ጎጂ ነገር ወይም በአውቶማቲክ መሣሪያ መጠቀም፤

ሰ) ለወፍ፣ ለኢንሹ፣ ለሚዳቋ፣ ለጥንቸል፣ ለቀበሮዎችና ለመሳሰሉት ትናንሽ የዱር ሕይወት ካልሆነ በስተቀር ካሊበሩ 0.22 በሆነ መሣሪያ መጠቀም፤

ሸ) ለትናንሽ ሣር በል የዱር ሕይወት ካልሆነ በስተቀር በነፋስ ጠብመንጃ ወይም በሽጉጥ መጠቀም፤

ቀ) ለሜዳ ፍየል፣ ለብሆር፣ ለዱኩላ፣ ለአምባራይሌና ለመሳሰሉት መካከለኛ የዱር ሕይወት ካልሆነ በስተቀር ካሊበሩ ከ0.240 እስከ 0.300 በሆነ መሣሪያ መጠቀም፤

በ) ለሣላ፣ ለቆርኬ፣ ለዱፋርሣና ለመሳሰሉት ትላልቅ የዱር ሕይወት ካሊበሩ ከ.300 እስከ .378 ባልሆነ መሣሪያ መጠቀም፤

DRAFT

ተ) ለጉሽ፣ ለጉማሬ፣ ለአንበሣ፣ ለነብርና ለመሳሰሉ በጣም ትላልቅና ኃይለኛ የዱር ሕይወት ካሊቤሩ ከ0.375 እስከ 0.600 ባልሆነ መሣሪያ መጠቀም፤

ቸ) በማንኛውም ዓይነት ተወርዋሪ ፈንጂ ወይም የእጅ ቦንብ መጠቀም፤

ኀ) ፈቃድ ሰጪው አካል በጽሑፍ ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውንም የዱር ሕይወት ለማደንዘዝ፣ ሽባ ለማድረግ፣ ለማፍዘዝ ወይም በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመስንከል የሚችል መድኃኒት ባለው ማንኛውም ዓይነት ተወርዋሪ መሣሪያ መጠቀም፤

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች ሥልጣን በተሰጣቸው ሠራተኞችና የተወሰነ ተግባር ለመፈጸም በፈቃድ ሰጪው አካል በጽሑፍ በተፈቀደላቸው ሰዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

## ክፍል አራት

## የዱር ሕይወትና የዱር ሕይወት ውጤቶች ሕጋዊ ባለይዞታነት

### 27. የባለቤትነት የምስክር ወረቀት

1/ ፈቃድ ሰጪው አካል በተወሰነው ፎርማት መሠረት ተሞልቶ ማመልከቻ ሲቀርብለት በሕጋዊ መንገድ የተገኘ የዱር ሕይወት ወይም የዱር ሕይወት ውጤት ባለይዞታ ለሆነ ሰው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡ በሳይተስ ለተመዘገበ ዝርያ በተጨማሪ የሳይተስ የምሥክር ወረቀት እንደስፈላጊነቱ ይሰጣል፡፡

2/ ማንኛውም ሰው በህጋዊ መንገድ የተገኘን የዱር ሕይወት ወይም የዱር ሕይወት ውጤት ለሌላ ሰው ሲሸጥ ወይም ሲያስተላልፍ የባለቤትነት የምስክር ወረቀቱን ለገዥው ወይም ለተቀባዩ ማዛወርና የባለቤትነቱ መብት መተላለፉንና ቀኑን በምስክር ወረቀቱ ላይ ማስፈር አለበት፡፡

### 28. የዱር ሕይወት ንግድ ፈቃድ

1/ የዱር ሕይወት ንግድ ፈቃድ ካልያዘ በስተቀር ማንኛውም ሰው በዱር ሕይወት፣ በዱር ሕይወት ውጤቶች ወይም በዱር ሕይወት ውጤት በተሠሩ ዕቃዎች ንግድ መሰማራት ወይም የዱር ሕይወት ውጤት በመጠቀም ልዩ ልዩ ቅርጾችን ማዘጋጀት፣ ትርኢት ማሳየት ወይም ሌሎች ቁሳቁሶች ማዘጋጀት አይችልም፡፡

2/ የዱር ሕይወት ንግድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በፈቃዱ መሠረት የሚያከናውናቸውን ተግበራት ሁሉ ፈቃድ ሰጪው አካል በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በመዝገብ እየፃፈ በተጠየቀ ጊዜ ለቁይይር ያቀርባል፡፡

3/ የዱር ሕይወት ንግድ ፈቃድ ተገቢው የማሳደሻ ክፍያ ተከፍሎ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

### 29. የዱር ሕይወትንና የዱር ሕይወት ውጤቶችን ወደ አገር ውስጥ ስለማስገባት

1/ የዱር ሕይወትና የዱር ሕይወት ውጤቶችን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የሚቻለው በተፈቀዱ የጉምሩክ መግቢያ በሮች ብቻ ሆኖ ከመጡበት አገር በሕጋዊ መንገድ መውጣታቸውን የሚያሳይ ማስረጃና የጤና ማረጋገጫ ሠርተፍኬት ሲቀርብ ነው፡፡

DRAFT

2/ በሳይተስ እዝሎች የተመዘገቡ የዱር ሕይወትን ወይም ውጤቶቻቸውን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ከመጡበት አገር የተሰጠ የሳይተስ ማውጫ ፈቃድ እንዲሁም በሳይተስ እዝል አንድ የተመዘገቡ ሆነው ሲገኙ በተጨማሪ ከባለሥልጣኑ የተሰጠ የሳይተስ ማስገቢያ ፈቃድ መቅረብ አለበት፡፡

3/ በአገር ውስጥ የሌሉትን የዱር እንሳሳት በነጻ በማስገባት ማርባት ይቻላል፤ ከዚህ እርባታ የተገኙትን የዱር እንስሳት ወደ ውጪ በሚልከበት ጊዜ የመውጫ ክፍያ ብቻ የሚከፍል ሆኖ ክፍያው በዓለም አቀፍ ዋጋ መሰረት ይተመናል፡፡

## 30. <u>የዱር ሕይወትንና የዱር ሕይወት ውጤችን ወደ ውጪ አገር ስለመላክ</u>

1/ ማንኛውም ሰው የዱር ሕይወትን ወይም የዱር ሕይወት ውጤቶችን ወደ ውጪ አገር ለመላክ፤

ሀ) የሕጋዊ ባለቤትነት የምስክር ወረቀት በማቅረብ ከባለሥልጣኑ የማውጫ ፈቃድ ማግኘት፤

ለ) ከባለሥልጣኑ በተሰጠው የመላኪያ ፈቃድ ላይ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች መጠበቅ፤

ሐ) በህግ የተወሰነ ማናቸውንም ተፈላጊ ክፍያና ቀረጥ መክፈል፣

መ) የዱር እንስሳው በሳይተስ ዝርያነት የተመዘገበ ከሆነ ከባለሥልጣኑ የሳይተስ ማውጫያ ፈቃድ እንዲሁም በሳይተስ ዕዝል አንድ የተመዘገበ ከሆነ ከሚደርስበት አገር የሳይተስ ማስገቢያ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

2/ የዱር እንስሳት በሕይወት ወደ ውጪ ሀገር ለመላክ የሚሠጥ ፈቃድ የሚያገለግለው ፈቃዱ ከተሠጠበት ቀን ጀምሮ ለ6 (ስድስት) ወራት ብቻ ይሆናል፤ ሆኖም የዱር እንስሳት ታድኖ ማርጣው ወደ ውጪ የሚላክ ሲሆን የመላኪያ ጊዜው ከታደነበት ቀን ጀምሮ በ3 (ሶስት) ወራት ውስጥ ዝግጁ ሆኖ መላክ አለበት፡፡

3/ የዱር እንስሳትን በሕይወት ማስመጣትና መላክ ለሚፈልግ ባለሀብት ሦስት ዓይነት የዱር እንስሳት በሕይወት የመነገድ ፈቃድ የሚሰጥ ሲሆን ዓይነቱና ክፍያው በዚህ ደንብ ሰንጠረዥ 3 ተራ ቁጥር 25 ላይ የተመለከተው ይሆናል፡፡

4/ ማንኛውም የዱር እንስሳትን በህይወት መነገድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የዱር እንስሳቱን ማጥመድ ወይም መያዝ የሚችለው ከጥበቃ ቦታዎች ውጭ በተፈቀደለት ቦታ ብቻ ነው፡፡

5/ ማንኛውም የዱር እንስሳትን በህይወት ለመያዝ የተፈቀደለት ሕጋዊ ሰው ከተፈቀደለት የዱር እንስሳት የማጥመጃ ወይም የመያዣ ቦታ ውጭ አጥምዶ ወይም ከተፈቀደለት የዱር እንስሳ ዓይነት ውጭ ሌሎች እንስሳትን ይዞ ቢገኝ ለፈጸመው ድርጊት ያጠመዳቸውን የዱር እንስሳት ዋጋን እጥፍ ከፍሎ እንስሳቱን በተያዙበት ቦታ መልቀቅ አለበት፡፡

6/ ማንኛውም ሕጋዊ የዱር እንስሳት አጥማጅ ለጠመዳ የተሰጠውን ፈቃድ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ሳያድስ ቢቀር ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡ ሆኖም አጥማጁ ግለሰብ ወይም ድርጅት እንደገና ፈቃድ ለማውጣት ከፈለገ የፈቃዱን ዋጋ እጥፍ መክፈል አለበት፡፡

## 31. <u>ወደ ሌላ አገር እንዲተላለፉ ስለሚደረጉ የዱር ሕይወትና የዱር ሕይወት ውጤቶች</u>

DRAFT

1/ የዱር ሕይወትና የዱር ሕይወት ውጤቶች የኢትዮጵያን ድንበር በማቋረጥ ወደ ሌላ አገር እንዲተላለፉ ለማድረግ፣

ሀ) የዱር ሕይወት ውጤቱ ከተላከበት አገር የመተላለፍ መብት የሚሰጥ ማረጋገጫና የጤና ማረጋገጫ ሠርተፍኬት ማቅረብ፣ እና

ለ) የዱር ሕይወት ወይም የዱር ሕይወት ውጤት የሳይተስ ዝርያ ከሆነ የሳይተስ ፈቃድ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

2/ የሳይተስ ስምምነትን ካልፈረመ አገር የሚመጣ የሳይተስ ዝርያ የዱር ሕይወት ወይም የዱር ሕይወት ውጤት የኢትዮጵያን ድንበር አቋርጦ እንዲያልፍ ፈቃድ አይሰጠውም፡፡

32. በሕገ ወጥ መንገድ ተይዘው የሚገኙ የዱር ሕይወትና የዱር ሕይወት ውጤቶች

1/ ማንኛውም ሰው በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘን የዱር ሕይወት ወይም የድር ሕይወት ውጤት ይዞ መገኘት፣ መነገድ፣ ወደ ውጪ አገር መላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ማስገባት አይችልም፡፡

2/ በሕገ ወጥ መንገድ ተይዞ የተገኘ የዱር ሕይወት ወይም የዱር ሕይወት ውጤት በቁጥጥር ሥር እንዲውል ተደርጎ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንዲወረስ ሲወሰን የፈቃድ ሰጪው አካል ንብረት ይሆናል፡፡

3/ በሕግ ወጥ መንገድ ተይዞ የተገኘ የዱር ሕይወት ወይም የዱር ሕይወት ውጤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት እንዲወረስ ሲደረግ የዋጋው ሠላሳ በመቶ ጠቋሚ ላስያዘው፣ አሥር በመቶ ለያዘው ወይም አርባ በመቶው ለጠቆመውና ለያዘው ሰው ይከፈላል፡፡

33. የዱር ሕይወት ውጤት አወጋገድ

1/ ማንኛውም የዱር እንስሳት ውጤት ከጥቅም ውጭ መሆኑ ሲረጋገጥ በአካባቢው ሕብረተሰብና ሥነ ምህዳር ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ በማያስከትል መንገድ እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

2/ የዱር ሕይወት ወጤት አወጋገድ ሂደት በፈቃድ ሰጪው አካል የተወከሉ ታዛቢዎች በተገኙበት መፈፀም አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

34. በሰው ሕይወትና በንብረት ለይ ጉዳት ስለሚያደርሱ የዱር ሕይወት

1/ የሰውን ሕይወት ለማዳን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዱር ሕይወት መግደል ወይም ማቁሰል ይህን ደንብ እንደመተላለፍ አያስቆጥርም፣ ሆኖም የተገደለው ወይም የቆሰለው የዱር ሕይወት ለሰው ሕይወት አደገኛ ለመሆን የቻለው ይህን ደንብ በመተላለፍ በተፈጸመው ተግባር ምክንያት ሆኖ ከተገኘ ደንቡን የተላለፈው ሰው ከተጠያቂነት ነፃ ሊሆን አይችልም፡፡

2/ ማንኛውም በንብረትና የሰው ሕይወት ላይ ጉዳት የሚያደርሱትን የዱር እንስሳት በመርዝ ከመጠቀም በስተቀር በዚህ ደንብ በተከለከሉ ዘዴዎች ጭምር ለመከላከል ይችላል፡፡

DRAFT

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የመከላከል ተግባር ከመፈጸሙ አስቀድሞ ለሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ አካል ማስታወቅ አለበት፡፡ ፈቃድ ሰጪ አካሉም ማስታወቂያው ሲደርሰው የታቀደው የማደን ተግባር እንዲታገድ በማድረግ በንብረቱ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ራሱ በሌላ መንገድ ለመከላከል ወይም ይህኑ ባለንብረቱ እንዲፈጽም ለማዘዝ ይችላል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የዱር እንስሳ የገደለ ወይም ያቆሰለ ሰው ይህንኑ በተቻለ ፍጥነት ለፈቃድ ሰጪው አካል ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ የአስተዳደር ወይም የፖሊስ አካል ማስታወቅ አለበት፡፡ ከአደን የተገኘው የዱር ሕይወት ውጤትም የሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ አካል ንብረት ይሆናል፡፡

35. <u>ስለ ቱሪስት አዳኝ ረዳቶች</u>

1/ ማንኛውም ሰው ቱሪስት አዳኝ ለመርዳት በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠው ፈቃድ ከሌለው በቀር ቱሪስት አዳኙ አስቀድሞ ያቆሰለውን የዱር እንስሳት ለማቁሰል፣ ለመግደል፣ ለመያዝ ወይም በዱር እንስሳው ላይ ለመተኮስ አይፈቀድለትም፡፡

2/ የቱሪስት አዳኝ ረዳት ያቆሰለው፣ የገደለው ወይም የያዘው የዱር እንስሳ ቱሪስት አዳኙ እንዳቆሰለው፣ እንደገደለው ወይም እንደያዘው ይቆጠራል፡፡

36. <u>የቆሰለ የዱር ሕይወትን ስለመከታተልና ሊደርስ የሚችል አደጋን ስለማስታወቅ</u>

1/ የዱር እንስሳ ያቆሰለ ሰው የዱር እንስሳውን ለመግደል የተቻለውን ሁሉ ጥረት ማድረግ አለበት፤ ሆኖም የቆሰለውን የዱር እንስሳ ለማደን ፈቃድ የሌለው ሰው ከሆነ የዱር እንስሳውን ተከትሎ የዱር ሕይወት ጥበቃ ቦታ ውስጥ ለመግባት አይፈቀድለትም፡፡

2/ ጐሽ፣ ዝሆን፣ ጉማሬ፣ ነብር ወይም አንበሳ ያቆሰለ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ዝርዝር ሁኔታዎች በመግለጽ በተቻለ ፍጥነት ለፈቃድ ሰጪው አካል ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ የአስተዳደር ወይም የፖሊስ አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

ሀ) የቆሰለውን የዱር እንስሳ ዓይነት፤

ለ) እንስሳው የቆሰለበትን ቀን፣ ሰዓትና ሥፍራ፤

ሐ) እንስሳው የተመታበትን ብልትና የቆሰለበትን የመሣሪያ ዓይነት፤

መ) የቆሰለውን የዱር እንስሳ ለመከታተል የተደረገውን ሙከራ፣ እና

ሠ) እንስሳውን ለማግኘትና ለመለየት የሚያስችሉ ሌሎች መግለጫዎች፡፡

37. <u>በዱር ህይወት ጥበቃ ቦታዎች ስለሚገነቡ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት</u>

1/ ባለሀብቱ የሚገነባው ሎጅ ወይም ማንኛውም የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋም ከዓመታዊ የተጣራ ትርፉ በዚህ ደንብ ሰንጠረዥ 1 በተመለከተው የብሔራዊ ፓርኮችና ዱር ሕይወት መጠለያዎች ምደባ መሠረት በምድብ አንድ ለተቀመጠው 6% /ስድስት በመቶ/፣ ለምድብ ሁለት 4% /አራት በመቶ/ እና ለምድብ ሦስት 2% /ሁለት በመቶ/ ለባለሥልጣኑ ይከፍላል፤

2/ ለባለሥልጣኑ የሚከፈለው ዓመታዊ ክፍያ በዓመቱ ሰኔ 30 ቀን በኋላ ባሉት 90 ቀናቶች ውስጥ ይሆናል፤ ክፍያው በተገለፀው 90 ቀናቶች ውስጥ ካልተፈጸመ በየወሩ የክፍያውን 10% እየጨመረ እንዲከፍል ይደረጋል፤

3/ ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግንባታ የሚፈቀድ መሬት ኪራይ ተመን በዚህ ደንብ ሰንጠረዥ 1 በተመለከተው የብሔራዊ ፓርኮችና ዱር ሕይወት መጠለያዎች ምድባ መሠረት በምድብ አንድ ለተቀመጠው በሄክታር 3000 /ሦስት ሺህ/፣ ለምድብ ሁለት በሄክታር 2000 /ሁለት ሺህ/ እና ለምድብ ሦስት በሄክታር 1000 /አንድ ሺህ/ ለባለሥልጣኑ ይከፍላል፡፡

## 38. የገቢ ክፍፍል

1. ባለሥልጣኑ በክልሎች ስር በሚተዳደሩት የዱር ህይወት መኖሪያ አካባቢዎች ላይ በውጭ ዜጎች ከሚከናነወኑት የዱር እንስሳት አደን፣ የዱር እንስሳት በህይወት ንግድ፣ የፊልም ቀረፃ እና የጥናትና ምርምር ተግባራት ከሚሰበሰበው ገቢ ላይ 85% የሚሆነውን ድርሻ ለሚመለከታቸው ክልሎች ያስተላልፋል፡፡
2. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ በህብረተሰብ አቀፍ የዱር ህይወት ጥበቃ ቦታዎች ላይ የሚሰበሰበው ገቢ ሙሉ በሙሉ ለሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ያስተላልፋል፡፡

## 39. ቅጣት

1/ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ሰው በአዋጁ እና በወንጀል ህግ ድንጋጌዎች መሰረት ይቀጣል፡፡

2/ በማንኛውም ሁኔታ ያለፈቃድ በዱር ሕይወት ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም የዱር እንስሳትን የገደለ በወንጀል ህጉ ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን የዱር እንስሳት የአደን ዋጋ ይከፍላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ እንዳይታደኑ በህግ የተከለከሉት የዱር እንስሳትን ተመንን በተመለከተ ባለስልጣኑ የዱር እንስሳው ዝርያ ዓይነት ላይ መሰረት አድርጎ ወቅታዊ ተመን ያወጣል፡፡

## 40. የተሻሩና ጸንተው የሚቆዩ ድንጋጌዎች

ስለ ዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የወጣው ደንብ ቁጥር 163/2001 ተሽሮ ሙሉ በሙሉ በዚህ ደንብ ተተክተዋል፡፡

## 41. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ………….. ቀን 2008 ዓ.ም.

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ጠቅላይ ሚኒስትር**

DRAFT